# የዳያስፖራ ሚና በአገር ቤቱ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ

ዱባለ ethio_nation@yahoo.com

የዚህ ጽሁፍ አላማ ማንኛውንም የተቃዋሚ ፖለቲካ ደጋፊን ለመደገፍ ወይም ለማንኳሰስ ሳይሆን በዲያስፖራ በኩል ያለውን ድክመት ለመጠቆም ነው። አሁን በዳያስፖራ የሚታየው የፖለቲካ ሁኔታ እንዳለ ከቀጠለ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ለአገራቸው ዲሞክራሲና ሕግ እንዲሰፍን የሚያደረጉት ጥረትና ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ሊያበረክቱ የሚችሉት እምቅ አቅም በየጊዜው እየተሸረሸረ ሄዶ ጭራሹን እንዳይዳፈን ከመስጋት የመነጨ ነው።

በአለፉት አመታት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትን የወያኔ ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ስንገመግም አንድ መሰረታዊ የሆነና ትኩረት ልንሰጠው የሚገባን እውነታ እናያለን። ይህም እውነታ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ተቃውሚ ፓርቲዎች ከዲያስፖራ ጋር በመሰርታዊ የፖለቲካ ፍልስፍና ለኢትዮጵያ ባላቸው ራእይ ቢግባቡም የፖለቲካ ታክቲክና ስትራተጂ አቀያየስና የትግል ስልት ምርጫ አደራረግ ላይ ግን ትልቅ ልዩነት እንዳለ መረዳት ይቻላል። እውነታው እንደሚያመለክተው ዲያስፖራ የሚያመነጨውን የትግል ስልት ወይም ኀሳብ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች እንዲቀበሉት ለማድረግ የማሳመን አቅሙ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተመናመነና እይኮሰሰ ሄዶአል። ይሄም በመሆኑ መሰረታዊና ትልቅ የሆኑ የትግል ውሳኔዎች ሲወሰኑ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙት የተቃዋሚ ፖለቲካ መሪዎች የዳያስፖራ አጋሮቻቸውን እይታና ግንዛቤ አያካትቱም። ይህ የሚያሳየው ደግሞ ዲያስፖራ በትግል ስልት መንደፍ ረገድ ያለው ተአማኒነት እየመነመነ መምጣቱን ነው። ይህም በዲያስፖራው ላይ ቅሬታዎችን ፈጥሮአል። ዳያስፖራው አገር ቤት ለሚካሄደው ትግል ወሳኝ ባይሆንም የድጋፍ ሚናው ግን ቀላል አይደለም።

ይህ በውጭ የሚኖረውን የፓርቲ ደጋፊዎችን በጎ ስሜት ከግምት ያለማስገባት ባህርይ በአንድ ፓርቲ ወይም በአንድ የፓርቲ መሪ ብቻ ላይ የሚታይ ነው ነው ብሎ ለመደምደም ያስቸግራል። እንደውም ቀጥሎ የምጠቅሳቸው ማስረጃዎች እንደሚያመለክቱት በአገር ውስጥ ያሉ የፓርቲ አመራሮች በውጭ ደጋፊዎቻቸው ላይ ያላቸው አመለካከት ተመሳሳይ ወይም አንድ አይነት እንደሆነ መረዳት ይቻላል። የዚህ አመለካከት ምንጭ ደግሞ የዳያስፖራውን ሚና ጠንቅቆ አልመንገንዘብ ወይም ደግሞ ዳያስፖራው ሃሳቡን ላማስፈጸም ወይም ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ የሚያደርገው ከመጠን ያለፈ ግፊት አሉታዊ አመለካከት ፈጥሮ ሊሆን ይችላል። ከዚህ እውነታ በመነሳት እንግዲህ ዲያስፖራ የእርምት እርምጃ መውሰድ ወይም ደግሞ የአገር ቤቱን ፖለቲካ ደጋፊ የሆነ አማራጭ የትግል ዘዴ መቀየስ ያስፈልገዋል።

ከላይ የተጠቀሰውን ሃሳብ ለመደገፍ የሚከተሉትን ቀላል ማስረጃዎች መመልከት ይረዳል። የ1997 ዓ.ም. ምርጫ ብንወስድ የምርጫው ሳጥን በወያኔ በመመዝበሩና በመጭበርብሩ፤ ኢትዮጵያውያን በድምፅ ብልጫ ለመረጡት ፓርቲ የወያኔ መንግስት ስልጣኑን እንደማያስረክብ ከተረጋገጠ በኋላ፤ የህብረት ፓርቲ ለፓርላማ የተመረጡት አባሎቹ የወያኔ ፓርላማ ውስጥ ገብተው እንዳይሳተፉ ወስኖ ነበር። ሆኖም ግን ይህን ፓርላማ ውስጥ ያለመሳተፍ ውሳኔ በመሻር ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት አባሎች በውጭ ያሉትን የፓርቲውን አመራር አባላት ሳያማክሩ ዶ/ር በየነና ዶ/ር መራራ ከሌሎች አባላቶቻቸው ጋር በመሆን ፓራላማ መግባታቸው ይታወሳል። ይህም በመሆኑ ታላቅ ተቃውሞና ቅሬታ በውጭ በሚኖሩ አባሎቻቸው ተሰምቷል።

በቅርቡ በ2002 ዓ.ም. የአንድነት ፓርቲ ወደ መድረክ ሲቀላቀል የመቀላቀሉን ውሳኔ ቀድም ብለው በውጭ ከሚኖሩ አባሎቻቸውን ደጋፊዎቻቸው አላማከሩም። ደጋፊዎቻቸውም ሆኑ አባሎቻቸው እንደማንኛውም ዜጋ ውሳኔ ከተፈፀመ በኋላ ከመገናኛ ብዙሃን ነው ውሳኔውን የሰሙት። ይህም ውሳኔ በከፊሉ ደጋፊ ላይ ቅሬታ ሲያሳድር በከፊሉ ደግሞ ውሳኔውን ሙሉ በሙሉ በመደገፍ ሳይሆን ሌላ ምርጫ በማጣታቸው ብቻ ውሳኔውን ለመደገፍ የተገደዱ ይመስላል። በተጨማሪም አንዳንድ የአንድነት ፓርቲ አባላት በስራ አስፈፃሚዎቹ የተወሰነውን ከመድረክ ጋር መቀላቀልና አንዳንድ መለስተኛ በሆኑ ጉዳዮች መግባባት መድረስ ባለመቻላቸው ምክንያት መከፋፈል ሲፈጠር ማንኛቸውም ማለትም ስራ አስፈፃሚውም ሆነ ተቃውሞ ያነሱት ወገኖች ውጭ የሚኖሩ አጋሮቻቸውን አላማከሩም። እንዲሁም የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) የምርጫ ስነምግባር የተባለውን ከወያኔ ጋር ሲፈራረም በውጭ የሚኖሩ ደጋፊዎቻቸውንና አባላቶቻቸውን አላማከሩም። የፓርቲው ደጋፊዎች እንዲሁ እንደማንኛውም ዜጋ ዜናውን ከመገናኛ ብዙሃን ነው ያገኙት።

የችግሩ መሰረታዊ ምክንያት በአገር ውስጥ የሚኖሩና በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በጂኦግራፊ ብቻ ሳይሆን የሚኖሩበት ህብረተብ የፖለቲካ ተመክሮና የባህል ሁኔታ የተለያየ መሆኑ ነው። በውጭ የሚኖሩና በአገር ውስጥ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በነዚህ (በጂኦግራፊና ባህል) አራራቂ ሁኔታዎች ተለያይተው እስከኖሩ ድረስ ከጊዜ በኋላ የፖለቲካ፣ የስነልቦናና የባህል ልዮነቶችን መፈጠር ብቻ ሳይሆን ልዩነቶቹ እየሰፉና እያደጉ መሄዳቸው ማንም ሊያቀመው የማይችል ሂደት ነው። በተለይም ደግሞ አንዳንድ ደካማ ወይም ተቀባይነት የሌላቸው የሚመስሉ ጉዳዮች በሰፊት እየታዩ ሲሄዱ ዳያስፖራው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያኖች ላይ የሚኖረው የማሳመንና ሃሳቡ ተቀባይነት እንዲኖረው የማድረግ ጉልበቱ እያነሰና እይተመናመነ ይሄዳል።

ማንም እንደሚያጤነው በስነልቦና በኩል አብዛኛው በውጭ የሚኖር ኢትዮጵያዊ በኢኮኖሚ የተሻለ ሆኖ በመገኘቱና በሰለጠኑ አገሮች በመኖሩ ብቻ በፖለቲካ አመለካከትም ሆነ በዘመናዊነት (ባህል) የበላይነት እንዳለው አድርጎ ራሱን ይመለከታል። ከዳያስፖራ ወደ ኢትዮጵያ ለጉብኝትም ይሁን ለስራ የሚጓዘውን አብዛኛው ኢትዮጵያውያን የሚያሳልፉበትና የሚያደርጉትን ድርጊት ብቻ ብንመለከት እያደገ የመጣውን የባህልና የስነልቦና ልዩነቶችን መረዳት ይቻላል። የኢኮኖሚ አቅሙ በመፍቀዱ ምክንያት ዲያስፖራ የሚውለው ሽራተን ወይም ሂልተን መሽትም ሲል በዲያስፖራ የተከፈቱ መጠጥ ቤቶችና አዝማሪ ቤቶች ሲሆን የሚያሳየውም ባህርይ አነጋገሩን ጨምሮ ከአገር ቤቱ ጋር የማይጣጣም አንዳንዱም ከመስመር የለቀቀ ነው። ይህ የአዋዋል ዘቤ በመሰረቱ መጥፎ ነው ማለት ሳይሆን አገር ውስጥ ነዋሪ በሆነው ህብረተሰብ በበጎ መልኩ ከሚታይበት ይልቅ በመጥፎ መልኩ የሚታይበት ሁኔታዋች አይለው ይታያሉ። ስለዚህም በአገር ውስጥ የሚኖሩት ኢትዮጵያውያን በአብዛኛው ድያስፖራን እንደሀገር ታላቅ ሚና የሚጫወት ሀይል አድርጎ ማየታቸው አጠራጣሪ ነው። ይህም እያደገ ያለው የባህል ልዩነት የፖለቲካ አመለካከት ላይም ልዩነት እያሳደረ አይሄድም ማለት አይቻልም።

በተጨማሪም ብዙ ተአሚነነት ያላቸው ጥናቶችና ቲዎሪዎች እንደሚያመለክቱት እንደ ወያኔ አይነት በአምባገነን የሚተዳደሩና በአደጋ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ አገር ውስጥ የሚኖሩ የፓርቲ መሪዎች የሚወስዱት የፖለቲካ ውሳኔና እርምጃ ከአሉት የትግል ውሳኔ አማራጮች ውስጥ ራሳቸው ላይ፤ ድርጅታቸው ላይና ደጋፊዎቻቸው ላይ ከፍተኛ ጉዳት የማያደርስውን አማራጭ እንጂ የግድ ከፍተኛ ውጤት የሚያመጣውን ብቻ አይደለም። ይህም የሚሆነው ባለማወቅ ወይም አላማቸውን በመክዳት ሳይሆን የሚኖሩበት የቀን ተቀን አደጋ የተሞላበት የፖለቲካ አካባቢ ስለሚያስገድዳቸው ነው። ይህ የውሳኔ አሰጣጥ ባህርይ በነፃ

አካባቢ ወይም አምባገነኖች ምንም የፖለቲካ ተፅዕኖ ማድረግ በማይችሉበት አካባቢ ከሚኖሩ የፖለቲካ ውሳኔ አሰጣጥ ባህርይ በጣም የተለየ ነው። በአብዛኛው በነፃ አካባቢ በሚኖሩ ፓርቲዎች የሚወሰዱ የፖለቲካ ውሳኔዎች ከአሉት አማራጮች ውስጥ የሚመርጡት ከፍተኛ ውጤት የሚያመጣውን ነው። ይህም የሚሆነው በብልሃት ወይም በጀግንነት ከሌሎች በልጠው ሳይሆን የአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ ስለሚፈቅድላቸውና አለአደጋና ፍርሃት መወሰን ስልሚችሉ ብቻ ነው። ነገር ግን በሁለቱም የውሳኔ አሰጣጥ ምንም ስህተት እንደሌለበት መረዳት ያስፈልጋል። በሌላ አነጋገር በሁለቱም አካባቢ ማለትም በነፃ አካባቢና በአደገኛ አካባቢ በሚኖሩት የፖለቲካ መሪዎች የሚወሰዱት ውሳኔዎች በየራሳቸው ከሚኖሩበት አካባቢ አንፃር ሲገመገም ትክክለኛ ወይም ለየፓርቲያቸው የሚያስገኙት ውጤቶች አመርቂ ናቸው ብሎ የሚያምኑበትን ነው።

ስለዚህ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የፓርቲ መሪዎችና በውጭ የሚኖሩ ደጋፊዎቻቸው ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በተደጋጋሚ በአንድ የፖለቲካ እሳቤ ላይ በየጊዜው የተለያየ የውሳኔ ሀሳቦች ላይ መድረሳቸው ብዙ የሚያስደንቅ አይደለም። በአገር ውስጥ የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች የሚወስዱት እርምጃ ነባራዊ ሁኔታውችን ማለትም ለግለሰቦች፥ ለራሳቸው ፓርቲ አባሎቻቸውና ለደጋፊዎቻቸው፤ ለፓርቲው፤ የሚያስከትለውን የማቴርያልም ሆነ በሰው ላይ የሚደርሰውን የአካል ጉዳት ያጤነና ጉዳቱን ለማስወገድ የሚያመቹ ዘዴውችን ያካተተ ነው። ርምጃውም የሚያስከትለው መዘዝና በጎ ውጤት ማመዛዘንና ርምጃውንም በተግባር ለመተርጎም በሚደረገው ጥረት በአገር ውስጥ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የተሻለ ግንዛቤ እንዳላቸው መረዳት ይገባል። ይህም ሊያስደንቀን አይገባም። ዲያስፖራው በውሳኔ አሰጣጥ ላይ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን አደጋ አገናዝባለሁ ብሎ ሊከራከር ቢችልም እንደ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳሉት ያህል እውቀትና ግንዛቤ ይኖረዋል ብሎ ለመናገር ግን አይቻልም።

ዳያስፖራው ታድያ ኢነዚህን አስገዳጅ የሆኑ ነገሮች ተገንዝቦ በአገር ውስጥ ለሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ፐርቲ መሪዋች ውሳኔ የሚያስፈልገውን እውቅና መስጠት እንጂ ተቃውሞ ብቻ በማቅረብ ውሳኔዎችን በሰላ ሂስ ማብጠልጠሉ ምንም ፋይዳ አይሰጥም። ውሳኔው ከዲያስፖራ ፍላጎት ውጭም ቢሆንም በትግስት መቀበል የግድ ይላል። ለውሳኔው ትክክለኛነት ምክንያታዊ ጉዳዮቹን ማወቅ ተገቢ ቢሆንም የፓርቲ መሪዎችን ሚና ለመተካት መሞከር ግን የስራ ድርሻንና አቅምን ካለመረዳት ባሻገር የአፍራሽነት ሚናው ያመዝናል። ዲያስፖራ ይህን ማድረግ ባለመቻሉ በአሁኑ ወቅት መፍትሄ በሌለው የተመሰቃቀለ ፖለቲካ ውስጥ ተዘፍቆ ይገኛል። ከሚጠበቀው በታች ራሱንም ዝቅ አድርጎ በመሰረታዊ ነገር ሳይሆን በጥቃቅን ጉዳዮች በተከፋፈሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቲፎዞ ሆኖ በስድብ ሲናቆር ይታያል። ይህ ከወያኔ ጋር የሚደረገውን ትግል ይጎዳዋል እንጅ አንዲትም ጋት ወደፊት አያራምደውም።

ዳያስፖራው የተዘፈቀበትን ውስብስብ ሁኔታውችን የመቀየር ሃላፊነትና ግዴታ አለበት። በአብዛኛው የዲያስፖራ ፖለቲካ መድረኮች ማለትም በፓልቶኮችና ድህረ ገጾች እንደሚታየው የተሳታፊው ሃሳቦች ጀብደኝነት የተሞላው ሆኖ መቀጠል የለበትም። በተለይም ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ላይ ግብረገብነት በጎደለው ስብዕናን የሚነካ የስደብ ውርጅብኝ የፖለቲካ መሪ ለመፍጠር የሚደረገውን ጥረት ያቀጭጨዋል። ራሱንም ደግሞ ከሚገባው በላይ አገር ወዳድነቱንና ጀግንነቱን በማጋነን ማወደሱ ፈጽሞ አስፈላጊ አይደለም።

በአጭሩ እነዚህ ማስረጃዎች የሚጠቁሙት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙት የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ውሳኔያቸው ከውጭ ካሉ ደጋፊዎችና አባሎቻቸው ተፅዕኖ ነፃ ማድረግ እንደሚሹ ነው። ዳያስፖራ ራሱን

እንደ አዋቂ የትግል ስልት አውጪ አገር ውስጥ ያሉትን ፓርቲዎች ደግሞ ስልቱን አስፈፃሚ አድርጎ መመልከቱ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ፖለቲካ ፓርቲዎች ዘንድ ተቀባይነት እንደሌለው በተደጋጋሚ በተደረጉት የፖልቲካ ፓርቲዎቹ ውሳኔ መረዳት መቻል አለበት። ሐቁ እንደሚጠቁመው የአገር ውስጥ የፖልቲካ መሪዎች ዲያስፖራን የሚመለከቱት ነባራዊ ሁኔታዎችን የማያገናዝብና ከአቅም በላይ የሆነ የትግል ሀሳቦችና ስልቶች የሚሰነዝር አርገው ሲለሚያዩት ከማማከር ይልቅ ማግለልን እየመረጡ የሄዱ ይመስላል። ይህ በአገር ቤት የሚገኙት የፓርቲ መሪዎች በነፃነት ውሳኔ መወሰን ከዲያስፖራ በገንዘብና በፕሮፓጋንዳ ሲደግፋቸው የቆዩቱን የፓርቲ ደጋፊዎች ትልቅ ቅሬታ ላይ መጣሉ አልቀረም። ስለዚህም ነው በተለያዩ የፓልቶክ መድረኮችና ድህረ ገጾች ላይ እንደሚታየው በጣም የጠነከረና ከመስመር የለቀቀ ስድብና ወቀሳ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ ፓርቲዎችና የፓርቲ መሪዎች ለይ ከዳያስፖራ ሲሰነዘር የሚታየው። ሆኖም ነገሩን በረጋ መንፈስ ካጤነው ግን የውሳኔ ልዩነት መፈጠሩ ሊደንቅን አይገባም እንደውም እንደሚከሰት ገምተን የውጭና የውስጡ ትግል የሚቀናጅበትና የሚደጋገፍበት አማራጭ መንገዶችን መፈለግ ይገባናል።

ዳያስፖራ የሚመኘውንና ማየት የሚፈልገውን በኢትዮጵያ ውስጥ ዲሞክራሲና ፍትህ የቶሞላበት ስርአት ማስፈን መሆኑ ይታመናል። በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትን የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለመደገፍ የግድ የፖለቲካ ፓርቲ የውስጥ ጉዳዮችና የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ጣልቃ መግባት የለበትም። ይህ ጣልቃ ገብነት ግጭትና መራራቅን እንጂ መቀራረብን አልፈጠረም። ስለዚህ ሌሎች የትግል መስኮች በዳያስፖራ ቁጥጥርና ውሳኔ ሊመሩ የሚችሉ ነገር ግን በአገር ውስጥ ላሉ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ድጋፍ እንጅ ጣልቃ ማይገቡ አማራጮች መፈለግና መሳተፍ ያስፈልጋል። ለምሳሌም ያህል የሲቪክ ድርጅቶች ማጠናከሩ በውጭ ያሉ ድርጅቶች ጋር በጎ ግኑኝነት መመስረቱና የወያኔን አምባገነናዊ አስተዳደር ማጋለጡ የተሻለ ውጤት ያስገኛል። የሲቪክ ድርጅቶችም ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር የሚጋጭ ሳይሆን የሚያስተሳስርና የሚደጋገፍ ፕሮግራም መንደፍ ይኖርባቸዋል። ዳያስፖራ እነዚህን የመሳሰሉ የትግል ስልቶች መቀየስና ያሉትንም ድርጅቶች ማጠናከር የማይችል ከሆነ አገር ውስጥ ካሉት የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር የነበረው የመተማመንና የመደጋገፍ ስልት እየተሸረሸረ ሄዶ ጭራሹን እንዳይጠፋ ያሰጋል።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!